# ዳግማዊ ሶሎሞን በሼራተን አዲስ

ነጻነት ዘገዬ

ዛሬ የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት ዋዜማ ነው፡፡ ከጓደኞቼ ጋር ስጫወት አምሽቼ ቤቴ ስገባ ቤተሰቤና ጎረቤቶቼ በኔ ቤት ውስጥ ቡና እየጠጡ በአዲስ አበባ ሼራተን የሚከናወነውን የፈረንጆች አዲስ ዓመት ዋዜማ የቀጥታ ዝግጅት በኢሕአዴግ ቲቪ እየተመለከቱ ደረስኩ፡፡ እኔም መቼም አያርመኝምና ከነሱ ጋር ለጥቂት ጊዜ ቁጭ ብል የሚያቅለሸልሽና የሚገለማ ዝግጅት ከዚያው የሃይቲ መንደር መቅረቡ ቀጠለ፡፡ እኔም መናደዴን ቀጠልኩ፡፡ ስለሃይተው ጉዳይ ካልተዘነጋኝ ዘቀቅ ሲል ማውሳቴ አይቀርም፡፡ ለማንኛውም በቅድሚያ እንኩዋን ለሁሉም በዓላት በሠላም አደረሳችሁ፡፡

ለአፍታ በተከታተልኩት የቀጥታ የዕብዶች የሚመስል ዝግጅት የታዘብኩትን ታዲያን ለናንተ ላስተላልፍ ተጣደፍኩ፡፡ እናም ብታጥርም እነሆ፤

ሔለን በርሔ ትባላለች ያሉኝ «ዘፋኝ» እንደቆርቆሮ እንደተንኳኳች ሁለት ዘፈን ያለ አንዳች የተመልካች ድጋፍና ጭብጨባ - ሊያውም የሞራል ግዳፍ ማለትም ድጋፍ ክፉኛ እንዳማራት በራስ ስሞሽ ተማጽኖ እንደለመነች - ተራዋን ጨርሳ ለባለተራው አኪረ ሰባራ ቀፎ ሞዛቂ በማስረከብ ከመድረክ ወረደች፡፡ በርስዋ ፋንታም ዳግማዊ ሶሎሞን፣ «የዜማ የቅኔ . . .የደጋጎች አገር» እያለ የተቀደደ ከበሮ በሚበልጠው ጎጋ ድምጽ  ይንኮራኮር ጀመር፡፡ መቼም ነገሩ ሲያልቅ አያምር እንዲሉ ነውና የሀገር አድባር ሳትከዳው በዚያ ዱሮውንም ቢሆን እንደነገሩ ወደን በተቀበልነው ግን ለክፉ የማይሰጥ በነበረ ድምጹ ስንትና ስንት ወጣቶችን እንዳላስጨፈረ የቱጃሩን ዕውቅ መሸታ ቤት በአንዴዉኑ ወደ ልቅሶ ቤትነት ለወጠውና አረፈው፡፡ እኔም ስለሱ አፈርኩ፡፡ እውነቴን ነው አንጀቴን በላኝ፡፡ በሀገራችን የገባ ሾተላይ መቼስ ልዩ ነው፡፡ ይዝብ እርግማን ወንጀለኞችን በሚያፋፋባት ሀገራችን አንዳንዴ እንደዚህ ዓይነት መጥፎ አጋጣሚዎችን መታዘብ ያልተለመደ አይደለምና የዚህ አርቲስት መዋረድ ከሕዝብ ልብ ተነቅሮ የመተፋት ውጤት ነው ቢባል ብዙም ስህተት የለውም፡፡ ንዋይ ለንዋይ ሲል እንዲያ ሲዋረድ ከማየት ዱሮ እንደማውቀው ወይ እሱ ወይ እኔ ቀድመን  ብንሞትስ? አልኩና የሁለታችንን ዕድል አማረርኩ፡፡ እሺ ፤ እሱስ ይቅር ይሁን ግዴለም ይቆይ፤ እኔ ብሞትለትስ? በእጅ አዙር የወያኔው ሼህ ክፍያም ይሁን በራሱ ከፍሎ የገባው ታዳሚ ሁሉ የዘመዱን ሞት የተረዳ ያህል - ንዋይ ሀብል ድምጹ እስኪበጠስ እያንቋረረ ጸጥ እረጭ ማለቱ ያስተዛዝባል፡፡ የሔልን ደግሞ ከንዋይም ይብሳል፤ ደግነቱ የርሱዋ ጊዜ ሕዝቡን አላሳዩንም፡፡ ይሄም መድልዎ መሆኑ ነው፡፡ የደበበ ልጅና የበርሔ ልጅ በወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር እኩል ቦታ የላቸውማ! ማፈሪያ የመንግሥት ሥርዓት ከማፈሪያ አሸርጋጅና አንፋሽ አጎንባሽ ዜጎች ጋር ሲገጣጠም እንደዚህ ያለ ጉድ ይታያል፡፡

ከሁሉም የሚያናድደው «ለዚህ ያበቁኝን እገልዬን እንዳልውጣቸው እግራቸው ይንጠለጠልብኛል፤ እንዳላዝላቸው ይከብዱኛል ሰውም ይስቅብኛል፤ ብቻ በጭብጨባ እኔን ሆናችሁና እኔን መስላችሁ አመስግኑልኝ» ማለቱ ነው፡፡ ዱሮውንስ ማን ከለከለው? ወንድሙ ሶሎሞን ተካልኝ የክህደት በሩን እስኪከፍትለት  ነበር የሚጠብቀው? ግን ግን እናንተዬ ዛሬ ድምጹ እንዴትና ለምን ከዳው? ወይንስ ዱሮውንም ቆርቆሮ ነበር? ከአንጅት ነው የምለው ዘፈነ ሳይሆን አለቀሰ ለማለት እንኩዋን አይቻልም፤ እንዴ? ስንትና ስንት የዱሮ አልቃሾችና ሙሾ አውራጆች እኮ በስንት ጣማቸው? ንዋይን ምን ነካው? ኢትዮጰያውያኑ የዘፈን አማልክት ከዱት ይሆን? በትናጋው ከመጡበት መቼስ ጉድ ነው! ግፍም ጭምር እንጂ ነው፡፡ በኢትዮጵያ እንደሆነ ሐመር መኪና ማከራየት አልተጀመረ ምን ሠርቶ ቤተሰቡን  እህል ዉሃ ያቃምሳል? ብትሰሙት እኮ እናንተም ታዝኑለት ነበረ፡፡ የምቀኝነት ብቻ እንዳይመስላችሁ፤ እውነቴንም ነው፡፡ ይህን የምለው ለምን እንደሆነ አንዳንዶች ነቄ ማለታችሁን እገምታለሁ፡፡

የሚገርመው ይህን መሰል ኳኳቴ ለማየትና ለማዳመጥ የሚከፈለው ገንዘብ የኔን የወር ደመወዝ እጥፍ ድርብ የሚያስከነዳ መሆኑ ነው - የኢትዮጵያ ብር 2000.00! ምግብና መጠጥ የሚጨምርና የማይጨምር መሆኑን ግን አታስዋሹኝ አልሰማሁም፡፡ ያለው ማማሩ ማለት እንዲህ ነው፡፡ ኑሮው

በየቀኑ ሸቅብ እየጓነ በአንዲት የድሆች ድሃ ሀገር በዋና ከተማዋ እምብርት ላይ ይህን የመሰለ አሥረሽ ምቺው መታዘብ ከግርምት በላይ ነው። ይሄ ሁሉ ገንዘብ በላብና በጉልበት ቢመጣ አይቆጭም ነበር፤ በላብ የሚመጣ ገንዘብም አልባሌ አይወጣም ተብሎ ይገመታል። ግን በአብዛኛው በዝርፊያና ንጥቂያ ነው። በጉቦና በማጭበርበር እንዲሁም ከህግ ውጭ በሚደረግ የንግድ ልውውጥም የሚግበሰበሰው ገንዘብ ቀላል አይደለም። ዘመኑ የብላ ተባላ ከሆነ በግምት 20 ዓመት ሊሞላን ነው። «ሥራ ምን ያደርጋል» ከተባለ ቆዬ። እኔ ሥንት ዓመት ነጋ ጠባ ሠርቼ ምን አተረፍኩ? ምንም! ድህነትና ጥቂት ልጆች ብቻ። ከሴቶቹ ልጆቼ ለአቅመ - ዱባይና ቤይሩት ቀድመው የሚደርሱትን ወይም ከወንዶቹ ልጆቼ ለአካለ - ሱዳንና ከተቻለም ለአቅመ-አሜሪካ የሚደርሱትን በደላላ ልኬ የጡረታ ዋስትናየን ለማስከበር ከማለም ውጭ በሀገሬ ምን ተጠቀምኩ? እኔ በመንግሥት መ/ቤት ተቀጥሬ ደመወዝ ስበላ በነበርኩበት ጊዜ ከዩንቨርስቲ የዜርፎር ካፌ አምልጠው ደደቢት በረሃ የገቡ አሠለጦች ቢሊዮኔር ሲሆኑ እኔ ከዱሮው ኑሮየ እጅግ ቁልቁል ተሽቀንጥሬ በምን ዓይነት አሣር ውስጥ እንደምኖር እኔና የላይኛው ነን የምናውቅ። ግን ይሁን - አላማርርም በሎሓል ያ ባለፕራዶ መኪና ዘፋኝ። ምነው ዛሬ በምቀኝነት ተለክፌ አመሸሁ ባካችሁ? ኤዲያ! «የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ» አሉ?

ሀገራችን እንደሃይቲ ከሆነች ሰነበተች። የሚቀረን እንደሃይቲ መሆን ነው። አትዘባርቅ እንዳትሉኝ። ነገሩ ወዲህ ነው። የሃይቲን ብሔራዊ ሀብት የሚቆጣጠሩት ከሕዝቡዋ ሁለት በመቶ ናቸው ይባላል። በአንጻራዊነት ጥሩ ኑሮ የሚኖሩት ደግሞ ከጠቅላላው ሕዝብ ከአምስት በመቶ አይበልጡም። ቀሪው 95 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ልክ እንደኛው የኑዋሪ አናኗሪ ነው - የሀብታሞቹን ችግር እዬተቸገረ፣ የሀብታሞቹን ድህነት እየደኸዬ አንድዬ ና እስቲለው ብቻ የሚንጠራወዝ ግዑዝ ቢጤ። በዚያ ላይ ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ የባዕድ አምልኮ ልክፍተኛ ነው። ሁሉም ተደማምሮ በምድሪቷ ላይ ተፈጥሮና አምላክ ተመሣጥረው ባስከተሉት መቅሰፍት ሳቢያ ባለፈው ዓመት የወረደባቸውን ዕልቂት ለመመልከት «ወርቃማ ዕድል» ልናገኝ  ችለናል - ያለ ክፍያ። ግን ማን ሊማር? የፈጣሪን ኃያልነትና የማይቀር ፍርድስ ማን ሊያስተውል? የሃጢያት ዋጋ ሞት ነውና ሃጢያት ላይ ወንጀልና ሙስና ሲታከልበት ምን ሊከተል እንደሚችል ከሃይቲ በላይ ሕያው ምስክር ሊኖር አይችልም። ስለዚህም ነው በምግባር እኛም የሃይቲን ሕዝብ እንደምንመስልና በቅጣት ግን በለዬለት መልኩ እንደነሱ ሊደርስብን የሚገባ ከፍተኛ መቅሰፍት መኖሩን ለማጠየቅ ስል ከፍ ሲል ቅኔ ቢጤ ልቀኝ የዳዳሁት - እንዳቅሚቲ። አውድማው ተለቅልቆ አልቆኣል፤ የሚቀረው ውቂያውና አዝመራውን እንደየአቅማችንና እንደየአስተዋፅዖዋችን የየመክሊታችንን መውሰድ ብቻ ነው።  ዛሬ የሚጨፍር ይጨፍር - ነገ መጨፈር አይኖር ይሆናል። ዛሬ የሚመዘብርና ድሆችን ራቁት የሚያስኬድ ይመዝብር ራቁታችንንም ያስኪድ - ነገ ይሄ ዕድል ላይኖር ይችላልና። ዛሬ በኔ ላብና ወዝ ሼራተንን ቀርቶ እንደደቡብ አፍሪካዊው የመጀመሪያው የሕዋ ቱሪስት ቱጃር እንደዴቪስ ቲቶ ጨረቃን ይጎብኝ - ነገ ይሄን ማለፊያ አጋጣሚ ላያገኘው ቢችል ጸጸቱ ከቅንጭላቱ ወይም ከጭንቅላቱ  አይወጣለትምና። የሚጨፍር ይጨፍር - የሚቆዝም ይቆዝም- የሚያለቅስም ያልቅስ፡ ሁሉም ዋጋቸውን አያጡም። ባለሐመሩ ወንድሜ ግን . . . እንደሠራ አይገድል አሉ? አይ ይህች አንድ እንጀራ? ከቶ ስንቱን ታሳይናለሽ? ለነገሩ ገና ምኑን ዐየንና? ማብቂያው ሲቃረብ ገና ብዙ አስገራሚ ሁኔታዎችን ልንታዘብ እንገደዳለን። አሁን ጊዜው በተለመደው ዓለማቀፋዊ ብሂል የፍጻሜው መጀመሪያ ቢባል አሳምሮ ያስኬዳል። «ይህን የክህደትና የእምነት ምክነት ዘመን በሽልም የሚያልፉ ጥንቁቅ ዜጎች ብፁዓን ናቸው፤ ከጽናታቸው አድማስ ባሻገር በዳግም ትንሣዔዋ የክብር አክሊል የምትቀዳጀዋን የወል ሀገር ታላቋን ኢትዮጵያ ይወርሳሉና» ይሉ ነበር ቀደምት አበው። ቃላቸው ሥሙር ይሁን፤ አሜን።

አንድ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤ «ገንዘብ እናትንና ሀገርን ብቻ ሳይሆን ራስንም ያስከዳል!» የትኛው መጽሐፍ? አታስዋሹኝ አሁን ከመሸ በሁዋላ ትዝ አይለኝም። ግን ከዚህ ይሰውር - በድጋሚ አሜን። ይሁንልኝ ያለ ይሆንለታል ይላልና መጽሐፈ ተዓምረ ማርያም - እንሥልሠው -  አሜን ይሁንልን!

netsanetzegeye3@gmail.com